የዘመኑ ትዉልድ

ትእይንት ፩

መጋረጃዉ ሲከፈት አንድ አባትና አንድ እናት ተቀምጠዉ ስለ ሴት ልጃቸዉ አጉል አወዳደቅ ይነጋገራሉ።

አቶ ደጀኔ ፡- እኔ እምለዉ ፀዳለ፡ ይህቺ ልጅ ምን እስከምቶን ነዉ የምትጠብቂዉ? ይሄዉ እንደ ወንድ የትም እያመሸች ነዉ የምትገባዉ ባሻት ጊዜ።

ወ/ሮ ፀዳለ፡- እንዴ? እርሶ አባቷ እያሉ እኔ ምን እንዳደርጋት ነዉ ታዲያ?

አቶ ደጀኔ፡- ቆይ አንቺ ተናግረሻት ስታበቂ ከአንቺ አልፋ ከሆነ ረጋ ብዬ እመክራታለሁ። በዚህ ክፉ ዘመን አንድ ልጃችንን በአዲሱ በሽታ አማካኝነት ከምናጣ እሾህን በእሾህ ነው አሉ ሴትን በሴት ነውና ይሻው አኔ ወደመኝታ ገብቼ ልተኛ ነው። ብታመሽም መምጣቷ አይቀርምና ምከሪያት። ጎሽ እንዲያዉም መጣች (ብለው ስትገባ ሁለቱም ቁጭ በለው ያይዋታል።)

ቆንጂት፡- (ኮስተር ብላ አለባበሷን አሳምራ አየተወጣጠረች ገብታ) ደህና አመሻችሁ አባዬ እማዬ? ብላትቀመጣለች። (እነሱም ለሰላምታዋ በእርጋታ ምላሹን ከሰጡ በኋላ)

አቶ ደጀኔ፡- በይ አንግዲህ ፀዳለ አንዳልኩሽ ይሁና። (ብለው አባትየው ተነስተው ወደ መኝታ ክፍላቸው ይሄዳሉ። እናትና ልጅ ብቻ ይቀራሉ።)

ወ/ሮ ፀዳለ፡- በይእስቲ ቆንጅዬ እራትሽን ወስደሽ ብይና የምንጫወተው ነገር ይኖራል። በይ ተነሽ እስቲ።

ቆንጂት፡- ምን አይነት ጨዋታ? እናንተ አራታችሁን በላች? አባዬ በልቷል? (ብላ በሷ ደግሞ እየተመነቃቀረችና አየተከሰታተረች እንጀራ ልታመጣ ወደ ጓዳ ገባች። እናትዬው ብቻቸውን ቁጭ ብለዋል።) እማ ቀይ ወጥ ብቻ ነው እንዴ ያለው? አይቡን ከምኔው ጨረሳችሁት። እማ እኔኮ ቅር ይልሻል ብዬ ነው እንጂ ጓደኛዬን ይዤልመጣ እከጅላለሁ (ብላ ሄዳ እንጀራ በሳሃን አምጥታ ፪ ቁርጥ ትበላለች።)

ወ/ሮ ፀዳለ፡- (እሷ እንጀራ ልታመጣ ወደ ጓዳ ስትገባ) አሁን እስቲ እንዴት ብዬ ላስረዳት? ያለችኝ ይህቺ አንድ ፍሬ ልጅ ናት ግን አጉል አወዳደቅ ወድቃ ከምትሞትብኝ ብነግራትስ። እነግራታለሁ እንግዲህ እያባበልኩ.....(ብለው ሲጨርሱ ቆንጂት ትመጣለች።)

ቆንጂት፡- እማ ብዙ እራት አላስፈለገኝም እናንተ በላችሁ አይደል።

ወ/ሮ ፀዳለ፡- አዎ ልጄ ጉረሻት እስቲ እሷን (እያሉ እሷ ዞር ስትል ይጨነቃሉ። እንጀራዋን በቁም ጎርሳ እየተሞላቀቀች ሰሃኑን እየጠጣች ባለችው ወኃ አለቃልቃ አስቀምጣ እናቷን ጠጋ ብላ ቁጭ አለች።እራሷን እያሻሸ) ቆንጂዬ አሁን አንድ ነገር ብነግርሽ ቅር ይልሻል? አባትሽንም ከምታሳዝኚ እሱም ከሚደነግጥብሽ አንድ ነገር ብንመካከርስ?

ቆንጂት፡- ምንድን ነው? ምን አጠፋሁ እማ? (እያለች ዘላ ትነሳና እንደመኮሰታተር ትላለች)

ወ/ሮ ፀዳለ፡- ቆንጂዬ ምን መሰለሽ አንቺ እንደ ወንድ ውጪ እያመሸሽ አባትሽ እንኳን በጊዜ ሰብሰብ ሲል ትንሽ ይከብዳል። አንቺ እንደ ሴቶች ወግ ከኔጋር ሰብሰብ ብትይ ምን ይመስልሻል።

ቆንጂት፡- እ... እማ ትላንት እኮ አንዱ ጓደኛችን ውጪ ስለሚሄድ ለሱ የአዳር ፕሮግራም/ሽኝት/ ተይዞለት ነው የቆየሁት ዛሬ ደግሞ አንድ ጓደኛዬ ሲያስጠናኝ ቆይቼ ነው አሁን የመጣሁት አባዬ ለዚያ ነው ፊቱ የተለዋወጠውና የወጣው እሺ ለሁሉም ብላ ዝም ትላለች።

ወ/ሮ ፀዳለ፡- እሱማ ምን ይቆጣል አልተቆጣም ተነጋገሩበት ብሎ ነው የወጣው ብላ ስትጨርስ መጋረጃው ይዘጋል።

ትእይንት ፪

መጋረጃዉ ሲከፈት አባት እናትና ልጅ ሆነው ይታያሉ ። አባት መንገድ ሊሄድ ነው። እናት ሻንጣ አዘገጃጅተዋል።

አቶ ደጀኔ፡- በይ እስቲ አፀዱ አኔ እንደምታውቂው ቀጠሮዬ መድረሱን ነግሬሻለሁ የዚህ የመሬቴን ነገር ፍርድ ቤት አንድ እልባት ላይ እስኪያደርስልኝ ድረስ እኔ መቀመጥ አይሆንልኝም። በይ አንችም የሴቶች እድር አለብኝ ብለሻል ሂጂ ወደ ስብሰባሽ።ቆንጅዬ በይ አንቺም ትምህርትሽን በርችልኝ ታድያ ይሄንን ውጪ ማምሸት ተወት አርገሽ... ኸ... የኔ ልጅ ቆንጅዬ ትምህርትሽን ጠበቅ። በይ አንቺ የውጪ 10 ብርፍርድ ቤቱ ይሄን ጉዳይ ይጨርስልኝ እንጂ ላንቺ አኔ ማደርገውን ታያለሽ። በሉ ቻው ብለው ትልቅ አባት መስለው ሄዱ።አናትም ወደ እድራቸው ሄዱ። ቤቱም ባዶ ሆነ። ቆንጂትም ሁለቱን ሽሽታ ስታበቃ፣ ደግሞ ሳሙኤል በመጣልኝ ትላለች።ጓደኛዋ ይሄን ጊዜ ቢመጣላት ፈቃዷ ነዉ።

ሳሙኤል፡- በሌላ መንገድ ብቅ ይልና። አቦ ቤተሰቦቿ ባይኖሩ ቀሽት ነበር ብሎ አለ። አለባበሱን አሳምሮ ይመጣል። በዚህ መሀል የሆነ ጨጩ ልጅ መንገድ ላይ ሲያገኝ ና እስቲ ማሙሽ ብሎ ጠርቶ እየዉ ቀስ ብለህ እዚያ ቤት ሂድና አንኳኩተህ ትጣራና ቆንጂት ሰዉ የፊልግሻል በልልኝ ስትመጣ ሳንቲም እሰጥሀለሁ ብሎ ሲልከዉ ሮጦ ሄደ ሲያንኳኳ ቆንጂት ብቅ ትላለች።

ቆንጂት፡- ምነው ማሙሽ ስትለው

ማሙሽ፡- ተልኬ ነው። ቆንጂት አንቺ ነሽ?

ቆንጂት፡- አዎ

ማሙሽ፡- እዚያጋ የቆመው ልጅ ይጠራሻል

ቆንጂት፡- ማነው? ሳሚ ይሆን እንዴ ብላ ብቅ ስትል እሱ ነው። አብራ ሌላ ትሆናለ